# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2014/07

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ መንግሥት ለስምንት የኢትዮጵያ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ አደረገ

### *በዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የግብርና ዕድገት መርሃግብር የእንስሳት ገበያ ልማት ፕሮጀክት አዲስ የገንዘብ ድጋፍ (ግራንት ፈንድ) ይፋ አደረገ*

***አዲስ አበባ፣ የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.*** - በዛሬው ዕለት በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት “በግብርና ዕድገት መርሃግብር የእንስሳት ገበያ ልማት ፕሮጀክት” ከስምንት ድርጅቶች ጋር የገንዘብ ድጋፍ (ግራንት ፈንድ) ስምምነት ተፈራረመ፡፡ በድምሩ ከ760,000 የአሜሪካ ዶላር በላይ ወጪ የተደረገባቸው ስምንቱ መጠነኛ የገንዘብ ድጋፎች፤ በኢትዮጵያ በእንስሳት ዕርባታ ዘርፍ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶችን እና የፈጠራ ስራዎችን ያበረታታሉ፡፡ አጠቃላይ ግቡም እንደ ቁም እንስሳት፣ ሥጋ እና ወተት ባሉ በተመረጡ የእንስሳት ዕርባታ እሴት ሰንሰለቶች ላይ ያለውን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ማሳደግ ነው፡፡

በተደረገው የገንዘብ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑት ስምንቱ ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አዲስ የእንስሳት ምርት እና ምርታማነት ማሻሻያ አገልግሎት
2. እመቤት እና ልጆቿ ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ኃ. የተ. የግ. ኩ.
3. ኢትዮ-ፊድ ኃ. የተ. የግ. ኩ.
4. ፕሮጀክት ሜርሲ
5. ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ.
6. ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ኃ. የተ. የግ. ኩ.
7. ዝማም ስንታየሁ ኢንተርፕራይዝ
8. ሃርሜ ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ኃ. የተ. የግ. ኩ.

የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ኢትዮጵያ ሚሽን ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር በመክፈቻ ንግግራቸው፤ ‹‹የኢትዮጵያ የእንስሳት ሃብት የከፋ ድህነትን እና የምግብ እጥረትን ለመቀነስ የሚያስችል ከፍተኛ አቅም አለው፡፡ የተደረጉት የገንዘብ ድጋፎች በአገር ውስጥ ስራ ፈጠራን ከማበረታታት ባለፈ፤ አዲስ እና የተሻሉ ምርቶችን በማምረት እና ለገበያ በማቅረብ ረገድ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን ለማስወገድ፤ ብሎም በእንስሳት ምርቶች ስራ ዘርፍ በርካታ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር ያግዛሉ፡፡›› ብለዋል፡፡

በዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የግብርና ዕድገት መርሃግብር የእንስሳት ገበያ ልማት ፕሮጀክት ግብ በወተት፣ ሥጋ፣ እንስሳት ዕርባታ፣ ማቀነባበር እና ወደ ውጪ መላክ ዘርፍ ምርታማነትን፣ ተወዳዳሪነትን፣ እና ትርፋማነትን ማሳደግ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በሚያደርገው በዚህ አዲስ የገንዘብ ድጋፍ ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት እስከ 5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚደርስ ገንዘብ መድቧል፡፡ ለአንድ ድርጅት የሚሰጠው ገንዘብም ከ25,000 እስከ 300,000 የአሜሪካ ዶላር ይሆናል፡፡ የሚደረገው ድጋፍ የሚወሰነው በአመልካቹ ፍላጎት እና በታቀደ ሥራ መሰረት ነው፡፡ የሚመረጡ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎች በዕሴት ሰንሰለቱ ከማምረቻ እስከ ገበያ ድረስ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የፈጠራ ስራዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ማበርከታቸውን ይቀጥላሉ፡፡

የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የግብርና ዕድገት መርሃግብር የእንስሳት ገበያ ልማት ፕሮጀክት በአሜሪካ መንግሥት ፊድ ዘ ፊውቸር መርሃግብር የሚደገፍ ሲሆን፤ ይህም የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት የግብርና ዕድገት መርሃግብር የሚያደርገው አስተዋጽኦ አካል ነው፡፡

###